አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ዘርፍ ለትምህርት አመራሩ የተዘጋጀ

አዲስ አበባ

# መግቢያ

ኤች አይ ቪ መከሰቱ ከታወቀበት እ.ኤ.አ ከ1981 ጀምሮ

- በዓለም አቀፍ ደረጃ

- ከ32.7 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን በኤድስ ምክንያት አተዋል

- 38 ሚሊዮን ሰዎች ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ኤችአይቪ በደማቸው እንደሚገኝ ይገመታል።

- በየዓመቱ 1.7 ሚሊዮን የሚሆኑ አዲስ በኤች አይ ቪ የሚያዙ ሰዎች  አሉ

- በየዓመቱ ከ690,000 ሰዎች ለህልፈት እንደሚዳረጉ መረጃዎች ያሳያሉ (UNAIDS FACT SHEET 2019) ።

# የቀጠለ...

❖ የሀገራችን

- የስርጭት ምጣኔ 0.93%
- 669,236 የሚሆኑ ወገኖች ኤች አይ ቪ በደማቸው ይገኛል፤(H
  ESTIMATES AND PROJECTION SPECTRUM, 201
  ያሳያል።
- 14,843 ሰዎች አዲስ በኤች አይ ቪ ተይዘዋል። ከእነዚህም ውስጥ
  - ✓67% የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ30 ዓመት በታች
  - ✓20% ዕድሜያቸው ከ20-24 ዓመት የሚሆኑ ወጣ ቶችና
  - ✓19% የሚሆኑት ከ0-4 ዓመት የሚገኙ ህጻናት ናቸው።

# የቀጠለ…

- ኤች አይ ቪ በአገራችን
  - ከክልል ክልል፣
  - ከአንድ ቦታ ሌላ ቦታ
  - በተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች
  - በከተማና በገጠር በከፍተኛ ደረጃ ይለያያል
  - የመያዝ ምጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚፈለገው መጠን እየቀነሰ እንዳልሆነ መረጃዎች ያሳያሉ።

# የቀጠለ...

## አዲስ አበባ

- አሁንም የኤች አይ ቪ/ኤድስ ጉዳይ የማህበረሰቡ የጤና የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ሆኖ ቀጥሏል።
- የስርጭቱ ምጣኔ 3.2 %
- 107,917 ሰዎች በደማቸዉ ዉስጥ ኤች አይ ቪ እንዳለባቸው ጥናቱ ያመለክታል፤
- በአንድ አመት ዉስጥ 1,408 አዲስ በኤች አይ ቪ የሚያዙ አሉ
- 1,879 የሚሆኑት ደግሞ በኤድስ ምክንያት ህይወታቸዉን ያጣሉ (በ2018 የስነህዝብ እና የዳሰሳ ጥናት/DHS )

# ኤች አይ ቪ እና ኮቪድ-19

# ኤች አይ ቪ

- ወረርሽኙን መግታት በበሽታው ሕይወታቸውን ላጡ 32.7 ሚሊዮን የዓለም ሕዝቦች ሲባል ከታሪካዊ ግዴታነትም በላይ ነው
- ለቀጣዩ ትውልድ
  - ✓ በጤናው ምቹ፣
  - ✓ እኩልነት የተረጋገጠባትና
  - ✓ ፍትኃዊነት የሰፈነባት ዓለም ለማስረከብ መሰረት መጣያ አጋጣሚ ተደርጎ ሊወሰድም ይችላል።
- የኤድስ ወረርሽኝን ማቆም መቻል ለሌሎች የጤናና የልማት ጥረቶች መነቃቃትን ይፈጥራል
- በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ሥራዎችን፤ በዘርፈ-ብዙ አጋርነት መርህ በአንድ ላይ ሆነን በትብብር መስራት ከቻልን ማሳካት የማንችለው ምንም ነገር እንደሌለ ማሳያ የሚሆን ነው።

# ኮቪድ-19

- በአሁኑ ወቅት የዓለምን ትኩረት በእጅጉ የወሰደበት ጊዜ ላይ እንገኛለን
- ወረርሽኙ እያስከተለ ያለውን ሁለንተናዊ ጫና ለመቀልበስ በሚደረገው ጥረት የኤች አይ ቪ ወረርሽኝ ቁጥጥር እና ኤድስ የህብረተሰቡ የጤና ችግር ወደ ማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ የተቀመጠውን ግብ ስኬት ወስኖታል፡፡
- የተባበሩት መንግስታት የኤድስ ፕሮግራም (UNAIDS) ወቅታዊ መግለጫ እንደሚያሳየው ጥምር የሆነው የኤች አ ይቪና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሊገታ የሚችለው
  - ✓ መድሎና መገለልን በመቀነስ
  - ✓ የሰው ልጆችን ማዕከል ያደረጉ ስልቶችን በመቀየስና
  - ✓ ሰብዓዊ መብቶችንና የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን መሰረት ያደረጉ ሁለንተናዊ ምላሾችን መስጠት ሲቻል መሆኑን ያስረዳል፡፡

# የቀጠለ

- የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፤
  - ✓ ኤች አይ ቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች፣
  - ✓ ሴቶችና ልጃገረዶች፣
  - ✓ ይበልጥ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች የነበሩባቸውን ችግሮች ይበልጥ እንዲባባስ አድር□ል

- የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በህብረተሰባችን ውስጥ የሚገኙ ስር የሰደዱ ልዩነቶች ጎልተው እንዲታዩ አድርጓል።

- ይህንን ተግዳሮት ወደ ጥሩ አጋጣሚ በመቀየር ነገሮችን ከወትሮ በተለየ መልኩ በትብብር ለማከናወን እንደ ማንቂያ ደወል ይሆናል።

ራሴን እና ቤተሰቤን ከኤች አይ
ቪና ከኮሮና ቫይረስ ለመከላከል
ተገቢውን ጥንቃቄ አደርጋለሁ!

# የ2013 ዓ.ም የመሪ ቃሉ ፅንሰ ሀሳብ

- በዓለም ዙሪያ ኤች አይ ቪ በደማቸው ለሚገኝባቸውና በቫይረሱ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ድጋፋችንን ለማሳየት
- በኤድስ ህይወታቸውን ያጡትን ወገኖች ለማስታወስ
- የዓለም ትኩረት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ
  - ✓ በጤና፣
  - ✓ በህይወትና
  - ✓ በኑሮ እያስከተለው ባለው ተጽዕኖ ላይ በማረፉ

# የቀጠለ

- የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከሌሎች ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች ለምሳሌ፡-
  - ✓ እኩልነት ከማስፈን፣
  - ✓ ከሰብአዊ መብቶች፣
  - ✓ ከፆታ እኩልነት፣
  - ✓ ከማህበራዊ ጥበቃና ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር እንዴት ጠንካራ ቁርኝት እንዳለው በማሳየቱ
- የአመራሩና የማህበረሠቡ ተሳትፎ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ ስኬት የማይተካ ሚና እንደነበረው ሁሉ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን በመግታቱ ረገድም ቁልፍ ሚና በመኖሩ

# የቀጠለ

- የማህበረሰቡ ንቁ ተሳትፎና ለጋራ ዓላማ በትብብር በኤች አይ ቪ/ኤድስ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች
  - ✓ መረጃ አገልግሎት፣
  - ✓ ማህበራዊ ጥበቃና
  - ✓ ተስፋ በመስጠቱ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳበረከተ ብዙ ተሞክሮዎችን በማየት

- ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ዓመት የዓለም ኤድስ ቀን **“ኤች አይ ቪን ለመግታት፣ ዓለም አቀፋዊ ትብብር ፣ የጋራ ኃላፊነት”** በሚል መሪ ቃል ይከበራል።

# የቀጠለ…

- ለጋራ ዓላማ መተባበር የማህበረሰቡ ኃላፊነት ብቻ ሊሆን አይገባም።
  - ✓ መንግስታዊ ተቋማት፣
  - ✓ ለጋሽ ድርጅቶች፣
  - ✓ የሐይማኖት መሪዎች፣
  - ✓ ሲቪክ ማህበራትና እያንዳንዱ ግለሰብ የኤች አይ ቪ ስርጭት በመግታት ጤናማና ለመኖር ምቹ የሆነች ሀገር በመገንባት ሂደቱ የማይተካ አሻራቸውን ማሳረፍ ይጠበቅባቸዋል።

# የቀጠለ

- የፖለቲካ ቁርጠኝነት
  - ✓ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለውጥ በመፍጠር መንግስታት ያስቀመጧቸው አዳዲስ ጠንካራ የፖሊሲ እርምጃዎችና ፈሰስ ያደረጉት መዋዕለ-ነዋይ የብዙዎችን ሕይወት ሊታድግ ችሏል።
- መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት መካከል ከፍተኛ ትብብር
  - ✓ በሀገራችን ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ የፀረ- ኤች አይ ቪ/ኤድስ ህክምና እንዳይቋረጥ የተደረገውን ሀገራዊ ጥሪ ተከትሎ የጤና ባለሙያዎችም ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል።
- እ.ኤ.አ በ2030 ኤድስ የማህበረሰቡ የጤና ችግር የማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ የመጨረሻዎቹ አስር ዓመታት ላይ ስለምንገኝ ከግቡ ለመድረስ ከዚህ በፊት ውጤት ያስመዘገብንበትን የአመራር ቁርጠኝነት መልሰን ማረጋገጥ ተተኪ የሌለው መፍትሄ ነው።

# የተመዘገቡ ውጤቶች

- ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ በጋራ በተደረጉ ጥረቶች፡-
  - ✓ በየዓመቱ አዲስ በኤች አይ ቪ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረበት በ46 በመቶ
  - ✓ በኤድስ ምክንያት የሚከሰትን ሞት በ52 በመቶ በላይ እንዲቀንስ ተደርጓል (FHAPCO,2019)።
  - ✓ **የኤች አይ ቪ ስርጭት ምጣኔ በ1990ዎቹ መጨረሻ ከነበረበት 3 በመቶ በ2017 ወደ 1 በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል (FHAPCO, 2019)።**
  - ✓ ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔ (በ6 ሳምንታት ውስጥ እና የጡት ማጥባት ጊዜን ጨምሮ) እ.ኤ.አ በ 2010 ከነበረበት 44 በመቶ እንዲቀንስ ተደርጓል (FHAPCO, 2019)።

# የቀጠለ...

- ✓ በ2019 የኤች አይ ቪ በደማቸው ይገኛል ተብሎ ከሚገመቱ ወገኖች መካከል 79 በመቶ የሚሆኑት ተመርምረው ራሳቸውን እንዲያውቁ ተደር□ል
- ✓ ከእነዚህ መካከል 90 በመቶ ያህሉን ደግሞ የፀረ-ኤች አይ ቪ መድኃኒት ላይ እንዲቀመጡና
- ✓ መድኃኒት ከሚወስዱት ውስጥ 91 በመቶ ያህሉን የቫይረስ ልኬት መጠን በሚፈለገው መጠን እንዲወርድ ማድረግ ተችሏል

# ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

## ተግዳሮቶቹ እርስ በርስ የተሳሰሩ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ፡-

- ✓ ከዚህ ቀደም ብሎ ለተመዘገበው የዘርፈ-ብዙ ምላሹ ስኬት ከፍተኛ ሚና የነበረው የአመራሩ ቁርጠኝነት ዛሬ ላይ መታየት አለመቻል
- ✓ የአመራር አደረጃጀቶች (ክበባት በሚፈለገው መልኩ አለመጠናከር)
- ✓ ተቋማት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ፕሮግራሞችን በባለቤትነት አለመተግበር
- ✓ ጉዳዩ የሚፈልገውን የሰውና የገንዘብ ኃይል በወቅቱ የማግኘት ተግዳሮት

# የቀጠለ…

- ይበልጥ ተጋላጭና ቅድሚያ የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮሩ እንደ የማህበረሰብ ንቅናቄና የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ያሉ የፀረ-ኤች አይ ቪ መከላከል ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች አለመጠናከር

- ኤች አይ ቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ራሳቸውን እንዲያውቁና አውቀውም ሕክምናውን እንዲጀምሩ ለማድረግ የሚያስችል ፍላጎት ከመፍጠር አንፃር ትልቅ ክፍተት መኖር።

# የቀጠለ

- ✓ አዲስ በኤች አይ ቪ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር በሚፈለገው መጠን መቀነስ አለመቻል

- ✓ የኤች አይ ቪ ምርመራ አገልግሎት በመንግስትና በግል የጤና ተቋማት እንዲሁም ማህበረሰቡ ድረስ በመዝለቅ እየተሰጠ የሚገኝ ቢሆንም አዲስ በኤች አይ ቪ የሚያዙ ሰዎችን ከማግኘት አንፃር የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ መሆን አልቻለም።

## የኤች አይቪ ምርመራ አገልግሎት በመንግስትና በግል የጤና ተቋማት

| ተ.ቁ | የበጀት አመት | እቅድ | ክንውን | ክንውን በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2010 | 9.2 ሚሊዮን (1.2%) | 73,981 | 0.8% |
| 2 | 2011 | 8.2 ሚሊዮን (1.2%) | 51,093 | 0.6% |
| 3 | 2012 | 7.8 ሚሊዮን (1.2%) | 41,070 | 0.5% |

# የቀጠለ

የአፍላ ወጣቶችና ህፃናት አፈፃፀም (እድሜያቸው ከ15 አመት በታች)

| ተ.ቁ | ፆታ | 2ኛው 90 | 3ኛው 90 |
|---|---|---|---|
| 1 | አፍላ ወጣት ወንዶች | 65 | 81 |
| 2 | አፍላ ወጣት ሴቶች | 74 | 83 |
| 3 | ህፃናት | 67 | 74 |

# የትኩረት አቅጣጫዎች

# የትኩረት አቅጣጫዎች

**የኤች አይ ቪ ፕሮግራሞች የሴቶችና የልጃገረዶችን መብትና የፆታ እኩልነት ያማከሉ እንዲሆኑ ማድረግ፡-**

- በትምህርት ተቋማት በማጠናከር በማጠናከርና ንቅናቄ በመፍጠር ለወረርሽኞች ምላሽ መስጠት
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ሴቶች እና ልጃገረዶች ተሳትፎ እና ውሳኔ የመስጠት ሚና ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- በየደረጃው የሚቀረፁ የኤች አይ ቪ ፕሮግራሞች አሳታፊና ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

“ኤች አይ ቪን ለመግታት፣ ዓለም አቀፋዊ ትብብር ፣ የጋራ ኃላፊነት”

**“Global Solidarity and Shared Responsibility”**

# አመሰግናለሁ!!